# ከእግዚአብሔር ፍቅር

“ … እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ::” (ኢሳ 48 ÷ 17)
God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. አዘጋጅ መላኩ ትዕዛዙ E-mail – hello@ethiogodslove.org

www.ethioGodslove.org ጥቅምት 1997 October 2004

ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ÷የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል
(ትንቢተ ኢሳይያስ 54÷13)



## መንገደኛ መላዕክት

ሁለት መላዕክት ወደ ሩቅ ሐገር ይጓዙ ነበር:: አንዱ ሽማግሌ ሌላኛውም ወጣት ነበሩ:: በመንገድ በመሸባቸውም ጊዜ አንድ ሐብታም ሰው ቤት ጎራ ብለው ለማደር ለመኑ:: ሐብታሙም ሰው ደግ ስላልሆነ÷ እንግዶቹን (መላዕክት) በእልፍኙ ውስጥ እንዲያድሩ አልፈቀደላቸውም:: ይልቁንም በምድር ቤቱ ውስጥ ያለምንም ምንጣፍ እንዲያድሩ ፈቀደላቸው::

መላዕክቱም በተፈቀደላቸው ምድር ቤት ወለል መኝታቸውን ሲያመቻቹ÷ ሽማግሌው መልዓክ ፊቱን ሲያቀና÷በግድግዳው ውስጥ አንድ ትልቅ ክፍተት አስተዋለ:: ተነሥቶም ክፍተቱን በተዓምር ደፈነው:: ወጣቱም መልዓክ:- ሽማግሌው መልዓክ የዚህን ጨካኝ ሰው ቤት መጠገኑ ገርሞት÷“ምን ማድረግህ ነው” ሲል ጠየቀው:: ሽማግሌውም መላክ:- “ሰው እንዲያይ እግዚአብሔር አያይም” ሲል መለሰለት::

በነጋታው ማልደው መንገዳቸውን በመቀጠል÷ ሲጓዙ ከዋሉ በኋላ መሸባቸውና÷ በአንድ ድኃ ገበሬ ቤት ለማደር ጎራ ብለው ለመኑ:: ገበሬውም በደስታ ተቀብሎ ያለውን እራት አቅርቦላቸው÷ አልጋውንም ለቆላቸው÷ በምቾት አሳደራቸው:: በነጋም ጊዜ መላዕክቱ ሲነቁ÷ ድኃው ገበሬና ባለቤቱ አምርረው ሲያለቅሱ አገኙአቸው:: የሚያለቅሱትም አንዲቱ አንጡራ ሐብታቸውና ወተት የምትሰጣቸው ላም በድንገት ሞታባቸው ስላደረች ነው::

በዚህ ጊዜ ወጣቱ መልዓክ እጅግ አዝኖ “ይህ ክፉ ነገር ሲሆን እንዴት ዝም ትላለህ?” ሲል ታላቁን መልዓክ ጠየቀው:: ደግሞ ቀጠለና: “ሐብታምና ንፉግ የሆነውን ሰው ቤት ግድግዳው ተነድሎ አይተህ ጠገንህለት:: ደግና ቸር የሆነው ድኃ ገበሬ ግን÷ ያለችው አንዲቱ ላሙ ስትሞትበት አይተህ ዝም ትላለህ” ሲል ሽማግሌውን መልዓክ ወቀሰው::

ሽማግሌው መላክ ግን አሁንም:- “ሰው እንደሚያይ እግዚአብሔር አያይም” ሲል መለሰለት:: ከዚያም ወጣቱ መልዓክ በሁኔታው መቸገሩን አይቶ እንዲህ ሲል ያብራራለት ጀመር::

“አየህ ወጣቱ:- በሐብታሙ ንፉግ ሰው ቤት ባደርን ሌሊት በደፈንሁት ግድግዳ ውስጥ ብዙ የወርቅ ክምችት ነበረበት:: እኔ ግን ሐብታሙ ሰው ንፉግ ስለ ሆነ÷ ወደ ፊት እንዳይባረክ ደፈንሁበት እንጂ እርሱን መርዳቴ አልነበረም:: እንዲሁም ባለፈው ሌሊት በደጉ ድኃ ገበሬ ቤት ተመችቶን ስናድር÷ የሞት መላክ የደጉን ገበሬ ባለቤት ለመውሰድ መጥቶ ነበር:: እኔ ግን ላሚቱን ወስዶ ሚስቱን እንዲተው አስገደድሁት::”

“አየህ ወጣቱ:- ነገር ሁሉ እንደሚመስለን የተገለጠ አይደለም:: አንዳንድ ጊዜ በፈርሐ እግዚአብሔር በሚኖሩት ሰዎች ላይ ክፉ ነገር ሲደጋገም÷ክፉዎች ግን የቀናቸው ሲመስሉ:- በሚታየውና በምትሰማው አትታለል:: ምክንያቱም እግዚአብሔርን ለሚወዱት ደጋግ ሰዎች ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን” “ሰው እደሚያይ እግዚአብሔር አያይምና፤ አለው ይባላል::



የእግዚአብሔር ሰው ሆይ:- የሚደርሱብህን ደስ የማይሉ ነገሮች አይተህ ጌታዬ ጥሎኛል አትበል:: ነገር ግን በዕምነት÷ ከደረሰብህ ሁኔታ ውስጥ የሚወጣልህን የአምላክህን በጎነት ተጠባበቅ:: የደረሰብህ ነገር አንተን በመጥቀምና አምላክህን በማስከበር እንዲፈጸም ጸልይ:: ጸልይ እንጂ በምንም አትመረር:: ምክንያቱም÷ ከዚህ ምን መልካም ነገር ይወጣል? የሚያሰኙ አንዳንድ ነገሮች ለምን እንደሚደርሱብን የሚገለጥልን በመጨረሻ ላይ ስለ ሆነ ነው:: ፈጽሞ በዚህ ዓለም ሳለን የማይገለጡ ነገሮችም ይኖራሉ:: “ሰው እንደሚያይ እግዚአብሔር አያይም”፤ የነገር ሁሉ ማሰሪያው ግን:-“እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን::” እግዚአብሔር ይመስገን:: (ሮሜ 8÷28)

**********

ይህንን አገለግሎት መደገፍ ጌታ ቢያሳስባችሁ ወይም የአድራሻ ለውጥ ብታደርጉ በሚከተለው አድራሻ ጻፉልን::

God's Love
P.O.Box 6734
Lee's Summit, MO 64064
USA ወይም በኢ- ደብዳቤ
hello@ethiogodslove.org

## አስቸጋሪ ሰው

(የዚህን መልዕክት ይዘት ካገኘንባቸው ጽሑፎች በአንዱ:- ሴሲል ያስቦርን በጻፈው:- ከሰዎች ጋር የመግባባት ጥበብ (The art of getting along with people) በተባለው እንዲህ የሚል ይገኛል:- 'ማኅበረ ሰብዓዊ ችግሮች በዕድሜ ወይም በማሕበራዊ ክፍሎች አይወሰኑም:: በማንኛውም ሥፍራ ሲከሰቱ የደስታ ጠንቅና የሐዘን ምንጮች ናቸው' ይላል:: የሚከተለው ለግልና ለማሕበራዊ ሰላም ሊጠቅም የሚችል ምክር ነው::)

“እገሌ አስቸጋሪ ሰው ነው” ሲባል ሰምተህ ታውቃለህ? የሌሎች ሰዎች አስቸጋሪነት ሲነገር ሰምተህ ስለ ራስህ አስበህ ታውቃለህ? አስቸጋሪ ሰው መሆንና አለመሆን እንዴት ይታወቃል?

* ከሰዎች ጋር በሚኖርህ የተለያዩ ግንኙነቶች ተመሳሳይ ችግር ደጋግሞ የሚከሰትብህ ከሆነ:-

* ያልተማከሩ ሰዎች በተለያየ ጊዜና ሁኔታ አስቸጋሪ መሆንህን ነግረውህ ከሆነ:-

* ወዳጆችህ አብዛኛውን ጊዜ÷ በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚተውህ ወይም የሚርቁህ ከሆነና ወዳጅ የማይጸናልህ ከሆነ:-

* ከሰዎች ጋር ያለህ ወዳጅነት÷ በአብዛኛው÷ ጥብቀትና ጥልቀት የሌለው÷ከአፋዊነት የማያልፍ ከሆነ:- ወዘተ

## አስቸጋሪ ሰው መሆንህን ብትረዳ ምን ታደርጋለህ?

* ስለ ራስህ ዕውነተኛ ማንነት (አስቸጋሪነትህን) አምነህ በመቀበል÷ ራስህን ሳትኰንን÷ ለመለወጥ ልብህን አዘጋጅ:-

* ስህተትህንና ጥፋትህን ለመቀበል ትጋ

* ወዳጆችህንና በባሕሪህ የተቸገሩትን ሰዎች ከልብ የሆነ ይቅርታ ጠይቅ:-

* ባሕሪህን ለመለወጥ ጌታ በገለጠልህ መጠን÷ ፈጥነህ ርምጃ ውሰድ:-

* ስለ ባሕሪህ ኃላፊነት ይሰማህ እንጂ ሁሉን ችግር በሌሎች ላይ አታሳብብ:-

* ለሚታምናቸውና ለምታከብራቸው ሰዎች ምክር ራስህን ስጥ:: እነርሱም ከባድ ነገር ቢመክሩህና ቢገስጹህ እንኳን ለመቀበል አታቅማማ:: (ታማኝ አማካሪዎቹን የሚሰማ ንጉሥ መንግሥቱ ትጸናለች::)

* በመጨረሻም:- ራስህን ለማረም በምታደርገው በዚህ ቅዱስ ጥረት ወቅት÷ ለዲያብሎስ ክስ እንዳትመች ተጠንቀቅ: ከአሁን ጀምሮ ጌታ ለሚገልጥልህ ነገር አትስነፍ እንጂ÷ስላለፈው ማንም ሊከስህ መብት የለውም:: ያለፈው ጉድለትህም ሆነ በደልህ (በንስሐ) በጌታ ደም ተሸፍኖአልና፤ ጌታ ይመስገን::

## አስቸጋሪ ሰው ላለመሆን ምን ይደረጋል?

* ሁሉን የሚገዛ ጌታ እንጂ አንተ ኣለመሆንህን በማወቅ ግትርነትን አስወግድ፤ አንዳንዴ ስለ ሰላም ለመሸነፍ ፍቀድ:: የእያንዳንዱን ዕለት ሕይወትህን መንፈስ ቅዱስ እንዲቆጣጠርልህ በየዕለቱ በጸሎት ጋብዘው:-

* ስለ ልዩ ልዩ ሰብዓዊ ባሕሪያትና ማሕበራዊ ግብብነት ከመጽሐፍ ቅዱስና ከሌሎችም መጻሕፍት ተማር:-

* መልካም አነጋገርንና የመግባቢያ ፈሊጦችን ከመጻሕፍትና ከአዋቂዎች ተማር

* ሰዎችን ሳታስቸግር ወይም ሳትጎዳ ማሳመን ወይም መግባባት የምትችልበትን ችሎታ ከመጻሕፍትና ከአዛውንት ገብይ:- መግባባት ማሳመን ብቻ ሳይሆን ሌላውን ማመንንም ያጠቃልላል::

* እንደ ርግብ የዋኅ÷እንደ እባብ ብልኅ ሁን:- ርኅራኄንና ጥብቅነትን በልካቸው መጠቀም ልመድ:-

* ከሰዎች ጋር ስትነጋገር÷ ራስህንም የሰዎቹንም አቀባበል አስተውል:-

* የመሻሻልህን ሁኔታ በዕውነትና በፍቅር ተከታትለው የሚያሳውቁህን በሕይወት የጐለመሱ የእግዚአብሔር ሰዎች ፈልገህ ተጎዳኝ:-

* ሁኔታህን ሁሉ በየዕለቱ ጸሎትህ ለጌታ ከማሳሰብ አትቆጠብ:: በየጊዜው በምታገኛቸው መሻሻሎች ጌታን ማመስገን አትርሳ:: እግዚአብሔር ሊረዳህ እንደሚደሰት ሁሉ÷ ምስጋናህንም መስማት ይሻልና::

---

## አራቱ ወቅቶችና ዛፉ

አንድ ሰው አራት ልጆች ነበሩት።እርሱም ልጆቹ ውሳኔ ለማድርግ ሆነ ፍርድ ለመስጠት እንዳይቸኩሉ ማስተማር ይሻ ነበር።

ስለዚህ እያንዳንዱ ልጅ አሩቀ ሐገር የሚገኘውን አንድ ፍሬ ሰጭ ዛፍ፥ በተራው በመሄድ እንዲጎበኝና ተመልሶ ያየውን እንዲገልጽ አስረድቶ ላከ።

የመጀመሪያው ልጅ በበጋ ወቅት ሄደ። ሁለተኛው ልጅ በበልግ፥ ሦስተኛው በክረምት፥አራተኛውም በጸደይ ወቅት ሄዱ። ሁሉም በየተራቸው ሄደው ከተመለሱ በኋላ በአንድነት ተገናኘተው ያዩትን ዛፍ ሁኔታ እንዲገልጹ አባትየው ሰበሰባቸው።

በበጋ ወቅት ዛፉን የጎበኘው የመጀመሪያው ልጅ ገለጻውን ሲጀምር:-"ያየሁት ዛፍ ጎስቋላ ፥ ጠማማና አስቀያሚ ነው" ሲል ተናገረ።

በበልግ ወቅት ዛፉን የጎበኘው ሁለተኛው ልጅ ግን በተቃውሞ ተነሣና:- "እኔ ደግሞ ያየሁት ዛፍ፥ቀጠሎቹ ያቆጠቆጡ፥ ልምላሚ የቃጣውና ተስፋ ያለው ዛፍ ነበር" አለ።

ቀጥሎም በክረምት ወቅት ዛፉን የጎበኘው ሦስተኛው ልጅ በተራው ገለጻውን ሲሰጥ:- "እኔ ያየሁት ዛፍ ልዩ ነው። ከላይ እስከ ታች በአረንጓዴ ቀጠሎች የተሸፈነ፥ባማሩ እምቡጦች ያሸበረቀ ነው፣ እኔስ እንዲህ የሚያምር ነገር አይቸም አላውቅ" አለ።

በመጨረሻም አራተኛው ልጅ ተነስቶ ሁሉንም ተቃወመ። "እኔማ ያየሁት ዛፍ የተለየ ነው። ከላይ አስከ ታች ለምለም፥ የበሰሉ ፍሬዎቹ ከሩቅ የሚያስጎመዡ፥ ጠረናቸውም ነፍስን የሚያድስ፥ የተመቸውና የተከናወነለት ዛፍ ነው።" ሲል በአድናቆት ተናገረ።

አባትየውም ሁሉንም በጥሞና ካዳመጠ በኋላ፥"ሁላችሁም ልክ ናችሁ"በማለት ማስረዳት ጀመረ። ቀጥሎም እያንዳንዳቸው ዛፉን ባዩበት ጊዜ፥ ያዩት ሁኔታ ዕውነት መሆኑንና ነገር ግን የሰውን ሆነ የዛፍን ሁኔታ በአንድ ወቅት አይታ መፍረድ እንደማይቻል አስረዳቸው። ምክሩንም ቀጠለና:- "የዛፍም ሆነ የሰው ልጅ ማንነት በድርቀቱ ወቅት ከፍቶትና ጠውልጎ ባለበት ጊዜ በሚታየው መልኩ ሊገመት አይገባም። እንዲሁም በበጋና በድርቅ ያልተፈተነውን፥በምቾትና በልምላሚ ወቅት ተቀማጥሎ በሚታይ ገጽታ ብቻ ላይ ተመሥርቶ ማድነቅ ስሕተት ነው። በተለይም የሰውን ልጅ ማንነት በሚመለከት:- በተለያዩ የሕይወትና የኑሮ ወቅቶች ውስጥ ሳናየው፥ ውሳኔ ላይ መድረስ ትክክል አይሆንም።

ራስንም በሚመለከት እንደዚሁ ነው። ምንም እንኳ አንዳንድ የሕይወት በጋና ድርቀቶች ተስፋ መቁረጥ ቢያሰኙም:- ታግሦ የዝናብን ወቅት ላለመጠበቅ ስሕተት ነው።

በበጋ ወቅት ተስፋ መቁረጥ:- የጸደይን ውበትና ተስፋ፥ የክረምቱን ልምላሜና የበልግን መከር ወቅት ሳያዩ ያስቀራል። ስለዚህ ሕይወት በክፉ ወቅት ብቻ ስለማይለካ፥ ክፉን ቀን በዕምነት ብንታገሥ፥ መልካም ወቅት በእርግጥ መምጣቱ አይቀርም ፤ እግዚአብሔር ይመስገን። በሐገራችን፥ በብዙ ሐገሮችም፥ አራት ወቅቶች አሉ። በጋ ሆኖ ሲቀር፥ ወይም ክረምት ሆኖ ሲቀር ታይቶ አይታወቅም። ቢፈጥም ቢዘገይም አንዱ ለሌላው ቦታውን መልቀቁ የእግዚአብሔር ሕግ ነውና ፤ እግዚአብሔር ይመስገን።

************

## ከሁሉ ውድ



## ነፃ ስጦታ

*የሕይወት ሚስጢር ከገባኝ ወዲህ ሁሌ የሚገርመኝ :- የዘላለም ሕይወት ነፃ የእግዚአብሔር ስጦታ ሲሆን÷ ጊዜያዊ ነገሮች ግን በልፋት መገኘታቸው ነው:: መጽሐፍም እንዲህ ይላል:-*

*"ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?"* *(ማቴ 16÷26)*

*"የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን፡ በክርስቶስ እየሱስ በጌታችን፡የዘላለም ሕይወት ነው::" (ሮሜ 6÷23)*

*"ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም::" (ኤፌሶን 2÷8)*

### ደኅንነት በመልካም ተግባር ሆነ በገንዘብ አይገኝም

*"ሲምዖንም በሐዋሪያት እጅ መጫን መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጥ ባየ ጊዜ÷ ገንዘብ አመጣላቸውና:-እጄን የምጭንበት ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ይቀበል ዘንድ ለእኔ ደግሞ ይህን ሥልጣን ስጡኝ አለ:: ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለው:-የእግዚአብሔርን ስጦታ በገንዘብ እንድታገኝ አስበሃልና ብርህ ከአንተ ጋር ይጥፋ::ልብህ በእግዚአብሔር ፊት የቀና አይደለምና ከዚህ ነገር ዕድል ወይም ፈንታ የለህም::"*
*(የሐዋሪያት ሥራ 8÷18-22)*

## የጊዜ ገደብ

*"በተወደደ ሰዓት ሰማሁህ፡በመዳንም ቀን ረዳሁህ ይላልና፤እነሆ÷የተወደደው ሰዓት አሁን ነው፤እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው::"*
*(2ቆሮንቶስ 6÷2)*
*"መከሩ አልፎአል÷በጋው ሄዶአል÷እኛም አልዳንነም::" (ት/ኤርምያስ 8÷20)*

## ድነሃል? አንቺስ?

*"ለሰዎች አንድ ጊዜ መሞት÷ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበላቸው÷..."*
*(ዕብራውያን 9÷27)*

### ጊዜው አሁን ነው

*"እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት÷ቀርቦም ሳለ ጥሩት÷ክፉ ሰው መንገዱን÷ በደለኛም አሳቡን ይተው፤ ወደ እግዚአብሔርም ይመለስ÷እርሱም ይምረዋል÷ ይቅርታውም ብዙ ነውና ወደ አምላካችን ይመለስ::"* *(ኢሳይያስ 55÷6-7)*

### እምቢተኛነት ኃጢአት ነው::

*"... እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው እንዴት እናመልጣለን?"*
*(ዕብራውያን 2÷3)*

*"እግዚአብሔርን የማያውቁትን÷ ለጌታችንም ለእየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል፤ በዚያም ቀን በቅዱሳኑ ሊከብር÷...በሚያምኑት ሁሉ ዘንድ ሊገረም ሲመጣ÷ (እምቢተኞች) ከጌታ ፊት፡ ከኃይሉም ክብር ርቀው በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ::"* *(2ተሰሎንቄ 1÷8-10)*

### ዛሬ ግን ተስፋ በደጅህ ነው

የእግዚአብሔር ፍቅር የሆነው ዘላለም ወዳጅህ ጌታ እየሱስ በዚህች ደብዳቤ÷ እንዲህ ይልሃል:: "እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ÷ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ÷ወደ እርሱ እገባለሁ ፤ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ፡ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል::" (ራዕይ 3÷20)

****************

እንዲህ ነው:: "እየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር÷ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና÷ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና÷በአፉም መስክሮ ይድናልና::"
(ሮሜ 10÷9-10)

## የደኅንነት ፀሎት:-

ጌታ እግዚአብሔር ሆይ:- ስጦታህ ነፃ ስለ ሆነ አመሰግንሃለሁ:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለተገለጠው ዕውነትህ ለመታዘዝ ዛሬ ቃል እገባለሁ::እየሱስ ጌታዬ መሆኑን በአፌ ለመመስከር አላፍርም:: ከሞትም አንዳነሣኸው አምናለሁ:: እርሱ ብቻ÷ አማላጄና አዳኜ መሆኑን አምናለሁ:: ስለዚህ እንደ ቃልህ ወደ መንግሥትህ ተቀበለኝ:: አሜን::

*ጻድቅና ታማኝ የሆንኸው ጌታ÷ ቅዱስ እግዚአብሔር ሆይ! ይህንን ጸሎት በዕምነት የጸለየች ነፍስ ሁሉ÷ በማይዋሸው ቃልህ መሠረት ÷ ወደ ዘላለም ሕይወት ተቀባይነት ስለተሰጣት አመሰግንሃለሁ:: በጌታዬ በእየሱስ ክርስቶስ ስም፤አሜን::*

### እየሱስ ጌታ ነው::
### ጌታ ይባርካችሁ::